ረቡዕ የካቲት 81998ዓም ( የፌብርዋሪ 15 2006).

# የፍኖት ዴሞክራሲ

## ሐተታ

## ጀምሮ ማቋረጥና እስከ ድል ፍፃሜ መታገል የተለየ ከስተት ነው::

ከሠላሳ ዓመታት በፊት የተጀመረውን ትግል ይዞ የቀጠለው ኃይል ተወደደም ተጠላ፥ ትግሉ ረዘመም አጠረ፥ መስዋዕቱ ከበደም ቀለለ ዓላማውን ከግቡ ሳያደርስ ትጥቁን እንደማይፈታ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ጠላት በበለጠ ደህና አድርጎ የሚያውቀውና የሚረዳው ወያኔ እንደሆነ ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው:: የውጭ ደጋፊዎቹ ሁሉ ወያኔን ከተቃዋሚዎቹ ጋር ውይይት እንዲያደርግ በጠየቁት ጊዜ ሁሉ የሚሰጣቸው መልስ ከኢሕአፓ በስተቀር ከሌሎች ጋር ለመወያየት ዝግጁ መሆኑን እንደሚገልጽላቸው እነርሱም አይደብቁለትም:: ወያኔም ይህንን መሳይ መልስ መስጠቱ አይፈረድበትም:: መራራውን ትግልና የተከፈለውን መስዋዕት በቀላሉ ረግጦ በተነሣበት ክቡር ዓላማ ላይ መደራደር የማይዋጥለት ኃይል ከወያኔ ጋር ለውይይት ቢቀርብ ምን ምን ነጥብ እንደሚያነሳ እራሱ ወያኔ አስቀድሞ ስለሚገባው፥ ይህንን ኃይል የወያኔ መሪዎች ፊት ለፊት ለመቅረብ ድፍረቱም ሆነ አሳማኝ ነጥብ አይኖራቸውም:: ዱባና ቅል አበቃቀሉ እየቅል እንደሆነ ሁሉ ወያኔና ኢሕአፓ በአፈጣጠር፥ በይዘት፥ በዓላማና ግብ የጨለማና የብርሃን ያህል ልዩነት ስላላቸው፥ ወያኔ ኢሕአፓን የሚፈርጅው በአጥፊና ጠፊ ደረጃ በመሆኑ አያስገርምም:: ከወያኔ ጋር የመሬት፥ የርስትም ሆነ የድንበር ክርክር የለም:: ከግለሰቦች ጋር ጠብም ይሁን ፍቅር አይኖርም:: ይህ ለወያኔ መሪዎች የሚተው ጉዳይ ነው:: እንደ ወያኔ በዘር ላይ ለተመሠረተ ፖሊሲ ስለማንታገል ከወያኔ ጋር የዘርም ሆነ የግለሰብ ጥላቻና ችግር የለብንም:: በዚህም ላይ ሊቸግራቸውና ሊጨንቃቸው የሚችለው አሁንም የመለስ ዜናዊን ቡድን ብቻ ይሆናል:: እኛ ከወያኔ ጋር ያለን ችግር መሠረታዊ በሆነው በኢትዮጵያ ሕልውናና በሕዝቧ አንድነትና ልዕልና ላይ ነው:: ይህ እስካልተመለሰ ድረስ ትግሉን መጀመር/ መፈጸም የሚባል ነገር አይኖርም::

ጭብጥ አሻሮ ይዘህ ስልቻ ሙሉ ቆሎ ወደቋጠረ ተጠጋ በሚለው ስሌት በመመርኮዝ ለዘሌቄታው የኢትዮጵያ ጥቅም ሳይሆን፥ ከጊዜያዊ ድግስ ለመቋደስ ተብሎ ትግሉን ማቋረጥ ሆነ በአጭር መቅጨት ሊታሰብ ባለመታሰቡ ጥያቄው በመጀመርና በመፈጸም ሊታይ አይገባውም:: እኩል የጀመረው ሁሉም እኩል ይፈጽማል ማለት አይቻልም:: መሠረታዊው ጥያቄ ሊሆን የሚችለው የትግሉ ዓላማና ግብ ዕልባት አግኝቷል? አላገኘም? ነው::

ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ተገቢውን መልስ እስካለገኘ ድረስ ትግሉን መቀጠል አጠያያቂ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የትግሉን ፍጻሜ የሚወስነው የዓላማው መሳካት እንጅ የትግሉ መርዘም ወይም የሚጠይቀው መስዋዕት ከባድነት አይደለም፡፡ በአስከፊ ሥርዓቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን የደቡብ አፍሪካን የነጮችን አፓርታይድ ፖሊሲን ለመገርሰስ ከሰባ ዓመታት የበለጠ ዘመን መጠየቁም፥ የመጨረሻ ግቡ አፓርታይድን አስወግዶ የዜጎቹን መብትና እኩልነት በሚያስከብር ሥርዓት ለመተካት ስለነበር፥ ዓላማው እስኪሳካ ትግሉ መቀጠል ነበረበት፡፡ የዛሬ ሠላሳ ዓመት ትግሉን የቀጠለው ትውልድም አሁንም በፅናት የሚታገለው ከዚህ መሠረታዊና ዓይነተኛ መርኅ በመነሳት ነው፡፡ በመሠረታዊ መርኅ ላይ ያልተገነባ ትግልም መልኅቅ እንደሌለው መርከብ ስለሚዋዥቅ የመሠረታዊ መርኅ ተገዥ መሆን ማለት የትግሉን መጀመሪያና መፈጸሚያ በሚገባ ተረድቶ ትግሉ ዒላማውን እስከመታ ድረስ በፅናት መታገል ማለት ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ሃቅ ለወያኔዎቹ ይረቅቅባቸው እንደሁ እንጅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ሀ ሁ ነው፡፡ ያለፉት ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን የኢትዮጵያን ዳር-ድንብር ከውጭ ወራሪ ኃይሎች ጠብቀው ያቆዩት ሳይሰለቹ፥ ሳይበገሩና ሳይንበረከኩ ያለማቋረጥ ሲታገሉ ስለነበር ብቻ ነው፡፡ የስድሣ ስድስቱ አብዮታዊ ትውልድም ይህን አኩሪ ጋሻ አንስቶ በፅናት ትግሉን መቀጠሉ ሊያስደንቅ ከቶ አይገባም፡፡ ሊያስገርምና ሊያሳዝን የሚችለው የተነሳበትን ክቡር ዓላማና ሀገራዊ ቃል-ኪዳን ዘንግቶ ተፍረክርኮ ቢቀር ነበር፡፡ በሌላ አኳያ ሲታይ ደግሞ፥ በየጊዜው እንደ ሁኔታው እንደ እንጉዳይ በቅለው የሚጠፉት ድርጅቶቹም የነበራቸውና ያላቸው ከባድ ችግር የፖለቲካ ትግል ውጤት በአንድ ቀን ጀምበር የሚገኝ ስለሚመስላቸው ጭምር ነበር/ነውም፡፡ ትግል ከጡረታ በኋላ የሚመስላቸውና ሁኔታ እየተጠበቀ በወረት የሚካሄድ እየመሰላቸው ብቅ ጥልቅ እያሉ የሚብተከተኩ ክፍሎች ሁልጊዜ የማይገነዘቡት ዓቢይ ጉዳይ ቢኖር፥ ኢትዮጵያን ቀስፎ ከያዛት ጥልቅና መሠረታዊ ችግር ነፃ ለማውጣት ሙሉ ሕይወትና ታላቅ መስዋዕት ማስፈለጉን ነው፡፡ ትግሉን ከዳር ለማድረስ በግድ ሳይታክቱ፥ ሳይደክሙ፥ ማቄን ጨርቄን ሳይሉና ለማንኛውም ፈተናና ችግር ሳይንበረከኩ በቀጣይነት መታገልን ይጠይቃል፡፡ የተጀመረው ትግል ዓላማው የተሳካ ሆኖ ግቡን እንዲመታ ካስፈለገ ቆራጥና የማይታክቱ ታጋዮች ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ ፈጣንና ተለዋዋጭ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ብሎ ለመክሰም ትግል እናካሂዳለን ብሎ መባከን ከአንድ ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ዳንኪራና የስሜት ማስተንፈሻ እፎይታ አያልፍም፡፡ ኢትዮጵያን ከዘረኝነት አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነፃ ለማውጣት፥ በግድ ኢትዮጵያዊ አይበገሬነት ባሕርይና ቆራጥነት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ለሁሉም ተሚልቶ እንደማይሰጥ ያለፈው ሠላሳ ዓመታት የትግል ተመክሮ ሕያው ምሥክር ሆኗል፡፡ ደራሲ ከበደ ሚካኤል አዝማሪና የውሃ ሙላት በተሰኘው ግጥማቸው አንድ ስንኝ ውስጥ "ያልሰማው ሲመጣ የሰማው ሲሄድ" እንዳሉት በዚህ የሠላሳ ዓመታት የትግል ሂደት ውስጥም አፍለኛው ሲመጣ የሰለቸው ሲሄድ መመልከት የተለመደ ክስተትና ትዝብት ሆኗል፡፡ ምንም እንኳን ትውልዱ ሁሉም በጠቅላላ ይህን ይጋራዋል ባይባልም፥ ይህ ደግሞ የአያሌ ሺ ዓመታት የበለፀገ ታሪክና ባሕል ካለው ሕዝብ አብራክ የወጣ ትውልድ ባሕርይ ሊሆን ባልተገባው ነበር፡፡ ያም

ሆነ ይህ፥ የተጀመረው ትግል ዓላማውን እስካሳካ ድረስ አስፈላጊው መሰዋዕት እየተከፈለ እንደሚቀጥል እንኳንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ጠላቶቹም ቢሆኑ ያለመጠራጠር ይቀበሉታል። ጀምሮ መተውና ፀንቶ መፈጸም የሰማይና የምድር ያህል ርቀት ስላላቸው፥ ጀምረው የተዉትን ጸንተው ለመፈጸም የቀጠሉትን ቢያንስ እንቅፋት ከመሆን ቢወስኑ ትግሉን እንደገፉት ይቆጠርላቸዋል።